የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

# ስማችን --- ኢወክንድ
# ልሳናችን---- ነቅንቅ

ቅፅ 1 ቁጥር 1 ኅዳር 2002 ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ መብትና ጥቅም አንደራደረም ብለው የተሠዉ ታላላቆቻችን እምቢኝ ለኢትዮጵያን ፈክረው ያለፉ አባት እናቶቻችን፤ አያት ቅድመ አያቶቻችን ዛሬ በእኛ ዘመን የደረሰ ውን ቢሰሙ ምን ይሉ ይሆን? የሚል ጥያቄ ተነስቷል፡፡

የገናና ታሪክ ባለቤት ኢትዮጵያ የፈጠረችን ልጆቿ ምን ተነካን? የሚል ጥያቄ ተጭሯል፡፡

ከወጣቱ ለወጣቱ--መልዕክት ይተላላፍ---

የአደንቁረህ ግዛው ወያኔያዊ ፖሊሲ ሰለባዎች የሆንን ወጣቶች ሰብረነው የወጣነውን የዘረኝነትን አሽከላ ዳግም ላንገባበት እርግጠኞች ነን፡፡ ባለፉት 18 ጨለማ ዓመታት ውስጥ ደቀን ያደግነው ወጣቶች በተስፋና በዕምነት በታጠረ ጧፍ ተፈላልገን ከተደራጀን እነሆ መንፈቃችን መጥቷል፡፡ በ 6 ወር ጉዞአችን ሰፍተናል፤ በቁጥርም በርክተናል፤ ድርጅታዊ ሥራችን--ዕድሜ ለቀደምቶቻችን እያልን -- በደማቸው ባስተማሩን ህቡዓዊ አሰራር አድማሳችን ሰፍቷል፡፡ ዛሬ ስንጮህ ላንሰማ፤ ብንነርት የማናደቅ ሆነን ልንታይ እንችላለን፡፡ ነገ ደግሞ ዚቁ ሲቀየር የሥያሜያችን ኢወክንድነት የኢትዮጵያ አለኝታ ክንድነትን አንደሚያስመሰክር ላፍታ ጥርጣሬ አይገባብንም፡፡

ዛሬ የቆመንበትን ዙሪያ ገባውን ስንፈትሽ፤ ጓዳ ጉድጓዳውን ስንቃኝ እመ ኢትዮጵያና ሕዝቧ የሲቃ ደወላቸው የሰቆቃ ጩኸታቸው ወክንድ ወክንድ የሚል ትርጓሜ ይሠጠዋል፡፡ ዕውነትም ተፈረጠመ የወጣት ክንድ ዛሬ ነው መፈክሩ፡፡

በአደባባይ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ጎንደር የተጨፈጨፉ ስጋዎቻችንን በደማቸው የተለቃለቀው ወያኔ፤

በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ ገብቶ ያረደው ወያኔ

በወጣት ተማሪ ጓደኞቻችን ደም የረሰረሰው ወያኔ

ወጣት እህቶቻችንን ያለርህራሄ ለባህር ማዶ የሸጠው ወያኔ

የአዋሳ ወጣት አርሶ አደሮችን በጥይት አረር የለበለበው ወያኔ

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

የኢሉባቦር ልጆችን እንደ ድኩላ አድኖ የጨረሰ ወያኔ

የኢትዮጵያ የምዕራብ በረኛችን የጋምቤላ ልጆችን ዘር ያጠፋ ወያኔ

የሀገሪቷን ሀብት ቀምቶ የደለበ ወያኔ

አርሶ አደሩን በግዳጅ ያፈናቀለው ወያኔ

ባልተመረመረ መርዝ ማዳበሪያ መሬታችንን ያመከነ ወያኔ

የአዲስ አበባን ነዋሪ በልማት ሰም የወረሰው ወያኔ

ዘረኝነትን አስፋፍቶ እርስ በርስ ያጫረሰው ወያኔ

የእኛ ወጣቶችን በውሸት ትምህርት ፖሊሲ ያደናቆረ ወያኔ

እነ ሽብሬ ደሳለኝን የበላ ወያኔ

15 ሺ ወጣት እስረኞችን በጭካኔ እያሰቃየ ያለ ወያኔ

የዴሞክራሲ ቀንዲል ለኳሾችን እነ ፀጋዬና ይስሀቅን አፍኖ ያጠፋ ወያኔ

በአጠቃላይ ምስጢረ ኢትዮጵያን ያረከሰ ሰይጣናዊ ስርዓት ዛሬ ደግሞ ብዙ ሚሊዮን ሄክታር ድንግል መሬታችንን ያለ ይሉኝታ ለባዕዳን በሽያጭ ሲያስረክብ እኛ ወጣቶች የምንሰጠው ምላሽና የምናስተላልፈው መልዕክት በከርሰ መቃብራችን ላይ እንጂ በውናችንስ አይሆንም ነው መልዕክቱ፤ አይሞከርም ይሆናል ምላሻችን፡፡ ከ 80 ሚሊዮን ሕዝብ የተፈጠርን ነንና በብሶቱ የተወለድን ኢወክንድ ነንና፤ በክንዳችን ኢትዮጵያችን ማዕረጓን እናስመልሳለን ነው የፈረጠመው ውሳኔያችን !

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ፤

የኢሕአፓ ወጣቶች ክንድ ድርጅት ኢወክንድ ሩቅ አሳቢ ግን ቅርብ አዳሪነትን ከኢሕአፓ ታላቆቻችን አልወረሰንምና ከወሬው ቀንሰን፤ ከስራው ደጉሰን ለመገኘትና ቅድስት ኢትዮጵያን ከር ኩሳን ለማላቀቅ ተደራጅተን ማድቀቅ ነውና ራዕያችን፤ ወጣቶች በያላችሁበት እየተደራጃችሁ ለማ ይቀረው ፍልሚያ በተጠንቀቅ ተዘጋጁ ይሆናል የዛሬው መልዕክታችን፡፡

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

አፄ ቴዎድሮስ በፍቅሯ ከንፎ ጥይት የጠጣላት ኢትዮጵያ፤

አፄ ምኒሊክ በእምነቱ እቴጌ ጣይቱ ብጡል በብልሀቷ ጠላቷን የመቱላት ኢትዮጵያ

እስላም ከክርስቲያን የተዋሀደላት እናት ኢትዮጵያ፤

ሺዎች አፍላ ዴሞክራሲያውያን የተሰዉላት ኢትዮጵያችንን ወደ ክብሯ ከፍ ለማድረግ የወጣቱ አስ ተዋፅዖ አይነተኛ መሳሪያ መሆኑን ተረድተን፤ ካለእኛም ካለ ልጆቿ በስተቀር አጋር አልባ የሆነ ችው ሀገራችን ከውስጥና ከውጭ ቅኝ ገዢዎች ለመላቀቅ የማትችል መሆኗን ተገንዝበን በያለንበት ትግሉን እናፋፍም ነው የዛሬው የኢወክንድ ጥሪ፡፡

መለስ ዜናዊና ኩባንያው ሀገራችንን ለህንድ፤ ለቻይና፤ ለአረቦችና ለሌላም ሌላም ሽጦ ለመጥፋት የሚያደርገው የጣር መወራጨት ኢትዮጵያዊ ክብራችንን ገሽልጦታልና ግጦ ሳይጨርሰን ይህን ስርዓት ለመገርሰስ ክንዳችንን እናጣምር እያለ ኢ ወክንድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

የኢትዮጵያን ድንግል መሬትንና የኢትዮጵያ አርሶ አደር መብትን በትግል እናስከብራለን!!!